ወርሃዊ ዲጂታል መጽሔት

ዙር ሠላሳ

መጋቢት፣ ፪፻፲፩ ዓ.ም



ENTERTAINMENT

#ልዩ ዳሰሳ

መዝናኛን በልዩነት- ያለእድሜ ገደብ

#ሃገርኛ

አቢሲኒያ ቫይን

ቫይን ለኢትዮጵያ

#አዲስ

ዮሐና

የመጀመሪያ አልበም

#ናፍቆት

ጉማ የፊልም ሽልማት

ለስድስተኛ ጊዜ

ሀበሻ ፋሲካ ኤክስፖ
HABESHA EASTER EXPO

THE BIGGEST EVENT IN ETHIOPIA

ከመጋቢት27-ሚያዚያ19
April 05-27

በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል
ADDIS ABABA EXHIBITION CENTER

ከ 500 በላይ
ተሳታፊ ድርጅቶች

ከ 500,000 በላይ
ጎብኚዎች



ከ100 በላይ
አገርኛና ወጣት
ሙዚቀኞች

30% እውነተኛ ቅናሽ

በርካታ
አዳጊ ሽልማቶች

የዳይኖሰሮች
ትዕይንት



አዘጋጅ

ሀበሻ ዊክሊ
HABESHA WEEKLY
Making Life Easy ...

9D CINEMA

FREE Wi Fi

Call Center 8022

በዚህ እትማችን

መጋቢት ወር፣ 2011 ዓ.ም.





5-11
#ልዩ_ዳሰሳ
GAST ENTERTAINMENT
መዝናኛን በልዩነት- ያለእድሜ ገደብ

12-14
#አዲስ
ዮሐና
የመጀመሪያ አልበም

15-17
#ናፍቆት
ጉማ የፊልም ሽልማት
ለስድስተኛ ጊዜ









21-25 #ዓለም

THE OSCARS

18-19 #ሃገርኛ አቢሲኒያ ቫይን

ዙር ሠላሳ

በዳሰሳ አዲስ ጎትመትና ማስታወቂያ ኃላ. የተ. የግል ማኅበር የምትዘጋጅ ወርሃዊ ዲጂታል መጽሔት ናት።
ጎዳር፣ 2011 ዓ.ም ተመሰረተ

ያግኙን

+251 924 312 097
addisaccess@gmail.com
ጉርድ ሾላ፣ ጂ እና ቢ ህንጻ 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 310

በመስመር ላይ (Online)

@AccessAddis
@AccessAddis


NEW ALBUM
COMING SOON



የዋና አዘጋጁ መልዕክት

ጤና ይስጥልኝ! የዛሬ ሰባት ወር ገደማ ለኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ ቋንቋ የምትዘጋጅ በመዝናኛ ላይ ብቻ ዲጂታል መጽሔት ለማዘጋጀት ስናስብ በምን መልኩ ? ምን አይነት ይዘት ያላት? በምን ያክል ጊዜ የምትወጣ? የሚሉት ጥያቄዎችን መመለስ ነበረብን እንዚህን ሁሉ ለመመለስ ከሞከርን በኋላ ግን ይችግረናል ብለን ያላሰብነው መጽሄቷን የመሰየም ጥያቄ ከፊታችን ተደቀነ። የአራት ቀናት የቤት ስራ ወስደን ብንሞክረውም ያልሳካው ጥሩ እና ሃገርኛ መልክን ለመስጠት የሚያመች ስያሜ የመስጠት ኃላፊነት በጋራ በተቀመጥንበት ጠረጴዛ ላይ ተወለደ። በሰላሳ ቀን ዑደት የምናወጣትን መጽሄታችንን ዙር ሠላሳ ብለን ሠየምናት።

ዙር ሠላሳ ወርሃዊ ከሆነችባቸው ምክንያቶች አንዱ በወሩ ውስጥ ያለፉና የሚመጡ ዝግጅቶችን ከመጠቆም ባለፈ በተለይ ደግሞ እኛ አዘጋጆቹ በአካል ተገኝተንና እያንዳንዱን ነገር ጎብኝተን የተደሰትንባቸውን የመዝናኛ አማራጮች ለናንተ ለተከታታዮቻችንም ማድረስ ነውና በተለይ በዚህ እትማችን ሰፋ ባለ ሁኔታ ይህንን አቅርበንላችኋል። በተጨማሪም እያደር እየሰፋ ያለውን የተከታታዮቻችን ብዛት መጽሄቷን በብዛት እንድትዳረስ ከማድረጉም በላይ ለእኛም አበረታች ሆኖናል።

ለዚህ ሁሉ ደግሞ እያመሰገንናችሁ ከእናንተ ጋር በምንገናኝባቸው መስመሮች ስንጠየቅ በነበረው መሰረት አዲስ በሆነ መካነ ድር /Website/ በቅርቡ ወደናንተ የምንደርስ ሲሆን ከጽሁፎች በተጨማሪ በምስልና ድምጽ የታገዙ በርካታ አዝናኝ ይዘቶችን ለማቅረብ ዝግጅታችንን እያጠናቀቅን መሆኑን በማክበር እንገልጽላችኋለን።

ዋና አዘጋጅ
ፍጹም ዓለማየሁ
addisaccess@gmail.com

አዘጋጅ
ኢሳያስ ሸፈራው
esoabi29@gmail.com

የገበያ ዳይሬክተር
ቴዎድሮስ ብርሃኑ
tediberhani@gmail.com

የሽፋን ፎቶግራፍ
በዳሰሳ አዲስ











GAST
ENTERTAINMENT MALL



#ልዩ ዳሰሳ

መዝናኛን በልዩነት
ያለእድሜ ገደብ







በምዕራባውያኑ አቆጣጠር በ1986 ታትሞ የወጣው የአሜሪካን ሀገር የሸማቾች ሪፖርት ላይ በወቅቱ ስለነበረው የገበያ ሁኔታ ሲናገር “አሜሪካ ‘ሞል-አዊ’ ሆናለች። ንጽሕናቸውንና ደረጃቸውን የጠበቁ ንፁህ አየር ያላቸው ሞሎች የአሜሪካ አውራ ጎዳናዎች ሆነዋል” (America has been "Malled." The "air-conditioned, sanitized, standardized" shopping malls "have become the new Main Streets of America") የሚል ነበር። የአሜሪካን ሀገር የሸማች ውሎ ብቻ ሳይሆን በጥቅሉ የአለምን የሸማቾች የለወጡት ሞሎች በየሰዉ ልብ ውስጥ የመዝለቃቸው ማሳያ ደግሞ ሆሊዉድ እንኳን በሚሰራቸው ፊልሞች ላይ እኔ አርኖልድ ሽዋዝንገር እና ቸክ ኖርስ ሞሎችን ከክፉ አድራጊዎች ጥቃት ሲከላከሉ ይታያል ይሄውም እነዚህ ቦታዎች ምን ያህል እንደጠቀሙና ለሰው ቅርብ እንደሆኑ ያሳያል።

ሞሎች እንደዚሁ አልተፈጠሩም። ጠቢባን የሆኑ አቃጆች በአንዲት ጀምበር እንዲህ እናድርግ ብለው በመፍጠር ፋንታ የማህበራዊ መስተጋብር ማዕከል እንዲሆኑ ያደረጋቸው ሰዎች ለመገበያየት, ባህልና አኑኗርን ለምጋራትና ለመነጋገር ሲሉ የፈጠሯቸው መሰባሰብያዎች በጊዜ ሂደት ሞል ወደመፈጠር እንዲበቃ አድርጎታል። አሁን ባለው የሸማች ባህል ከነዚህ ሁሉ ደረጃዎች አልፈው ሞሎች የህዋ ማዕከል ሊባሉ በሚችሉበት ደረጃ ደርሰዋል።

ከዘጠኝ አመታት በፊት በ2010 በተወሰደ መረጃ መሰረት በአሜሪካን ሀገር ብቻ 10,967 ሞሎች የነበሩ ሲሆን ይህ ቁጥር ከ9,300 እስከ 18,500 ካሬ ሜትር ላይ ብቻ ያረፉ ሞሎችን በመቁጠር የተገኘ ነው። ይህ ከፍተኛ የሆነ አመታዊ ገቢ የሚያስገኙ ሞሎች መስፋፋት የግዥ ስርዓትን ማሳለጥ ብቻ ሳይሆን በዚህ ሂደት ውስጥ የተጠቃሚዎችን ምኞት





ለመጠበቅ ሲባል የተለያዩ መዝናኛዎ ወደማካተት ብሎም ደግሞ ከሸመታው እኩል በሆነ መልክ ሲንማዎችን, የመዋቢያ ቦታዎችን, ካፍቴሪያና ሬስቶራንቶችን, የልጆች መጫወቻና ሌሎችንም የጊዜ ማሳለፊያና የመዝናኛ ምርጫዎችን ወደማቅርብ ሲሸጋገር ጊዜ አልፈጀበትም።

በሀገራችን በኢትዮጵያም ከመዲናችን ከአዲስ አበባ ውጭ እምብዛም የማይታዩት ሞሎች አዲስ አበባ ላይም ቢሆን በጣት ሊቆጠሩ የሚችሉ ናቸው። እነዚህ ሞሎች ካለው የተጠቃም ፍላጎት ጋር ብዛታቸው እንዲሁም መጠናቸው የተመጣጠነ ባለመሆኑ በተለይ በሳምንት የእረፍት ቀናት ወደ እነዚህ ስፍራዎች መሄድ ከገጠው ብዛት እንዲሁም መዝናናም በተደራቢነት የተካተተ በመሆኑ ለመዝናናት ከሚመጣው ሰው መብዛት ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ግርግር የሚፈጥር ሆኖ ከርሟል። ለዚህ ደግሞ ትክክለኛው መፍትሄ የሚሆኑት ለተለየ አላማ ብቻ የሚዘጋጁ ሞሎች ናቸው። እናም ታዲያ ለከተማችን አዲስ የሆነውና በቅርቡ ተከፍቶ አገልግሎት መስጠት የጀመረው የጋስት ኢንተርቴይመንት ሞል ለመጀመሪያ ጊዜ ከልጆች እስከ አዋቂ ድረስ ሊዝናኑባቸው የሚችሉ አማራጮችን ይዞ ሲቀርብ እናም በይፋው የመክፈቻ ስነ ስርዓቱ ላይ ታድመን ያየነውን ማካፈል ተገቢ መስሎን ስላገኘነው እንዲሁም ለተከታታዮቻችን አዳዲስ የመዝናኛ አማራጮችን መጠቆምም ስለሚገባን ለዚህ እትማችን የልዩ ዳሰሳ ርዕሰ ጉዳይ አድርገነዋል።

የልጆች መጫወቻ

በጋስት ኢንተርቴይመንት ሞል ላይ ለመስተናገድ ሲገቡ ለእርስዎ ብቻ ሳይሆን ልጆችዎንም የሚያስደስቱባቸው

አማራጮች በሰፊው ቀርበዋል። እነዚህ የልጆች መጫወቻዎች የተለያዩ እሌክትሮንክስ መሳሪያዎችን ያካተቱና እድሚያቸው ከሶስት ዓመት በላይ የሆኑ ሕፃናትን ለማዝናናት ተዘጋጅተዋል ከሁለተኛው ፎቅ ጀምሮ የተዘጋጁት የሕፃናት መጫወቻዎች ከተለያዩ በስክርን ላይ ከሚያዩ ወድድሮች እንዲሁም ሱሙሌተሮች ጀምሮ ሰፊ የሆኑ ሕፃናት ሊሮቱባቸው ሊዘሉባቸው እንዲሁም ሊንሸራተቱባቸው የሚችሉ አማራጮችን አቅርበዋል።

ለልጆች ብቻ ባልተወሰነ መልኩ አዋቂዎችም ሊሳተፉበት የሚችሉት እና አራተኛ ፎቅ ላይ የሚገኙት የሌዘር ታግ እና የሚረር ሜዝ ጨዋታዎች ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ አገልግሎት ላይ የዋሉ ሲሆን ልጆችዎን ይዘው ማጫወት ብቻ ሳይሆን አብረዋቸው ሊዝናኑባቸው የሚችሉ አማራጮችን አቅርበዋል።

“የኒንጃ ኮረኛ”

ብዙዎቻችን በቴሌቪዥን ስክሪኖቻችን የአሜሪካ ኒንጃ ዎርየር ዝግጅቶችን አይተናል። በዚህ ውድድር ላይ

#ልዩ_ዳሰሳ

ተወዳዳሪዎቹ ሙሉ የሰውነት ጥንካሬንና ብቃትን የሚፈትኑ የመዝለል፣ የመንጠልጠል፣ እንዲሁም ሙሉ የሰውንት ክብደትን ተሸክሞ በመንጠላጥያ ሐዲድ ላይ የመንሸራሸር ፈተናዎችን ለመወጣት የሚያደርጉትን ጥረት ተከታትለናል። ይህ በማይሆንበት ወቅት ደሞ ተወዳዳሪዎቹ ወደ ውሃ ውስጥ ሲወድቁና ከዚያም ለመውጣት በመዋኘት ሲታገሉ መመልከት ለተወዳደረውም ፈተና ለተመልካቹም ደስታን የሚያጭር ነው።

በጋስት ኢንተርቴይመንት ህንፃ ላይም ይህንኑ ሁኔታ በሚመስል መልኩ የተዘጋጀው ኒንጃ ዎርየር መጫወቻ ይገኛል። ከዚሁ አጠገብም የ “Rock Climbing” Simulation በተለያየ መልኩ ተዘጋጅቶ ከሰዓት ቆጣሪ ጋር ሰዎች እንዲወጡበት ይጠብቃል።

የማምለጫ ክፍል

Escape room ወይም የማምለጫ ክፍል የሰውን





የማሰብና የማመዛዘን ችሎታን ይፈትናል በአብዛኛው የአይ ኪው ፈተናዎች ላይ የምናያቸውን ፈተናዎች አይነት የያዙ ክፍሎች የተለያዩ እንቆቅልሾች በክፍሎች ውስጥ እንዲካተቱ በማድረግና የአመክንዮ እንዲሁም የመመልከትና የማገናዘብ ፈተንናዎችን በማካተት እያንዳንዱን ደረጃ የሚያልፉ ደግሞ ካሉባቸው ክፍሎች ውስጥ ያሉ ፍንጮችን በማፈላለግ በሚፈቀደው ሰዓት ውስጥ ከክፍሉ በመውጣት የሽልማቶች አሸናፊ የሚያደርጉ ናቸው።

እነዚህ አምስት ክፍሎች የተለያዩ አምስት ክፍሎችን የያዙ ሲሆን ከግብፅ ጥንታዊ የመቃብር ቦታ ጀምሮ የህዝብ ሽንት ቤትን, አዳኝ ያለበትንና ብዙ ክፍሎች ያሉትን መኖሪያ ቤትና የኮንጎ ጫካ ውስጥ መጥፋትን ያምያሳስቡ አምስት አይነት ክፍሎች አሉት። በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ እንደ ክፎሎቹ የስፋት መጠንና እንደ እንቆቅልሾቹ ክብደት መሰረት በማድረግ ከሁለት እስከ ስምንት ተጫዋቾች ራሳቸውን ሊፈትኑበት ይችላሉ።

ጅምናዚየም

በህንፃው የመዳረሻ ወለል ላይ በርካታ ቋአሚ ብስክሌቶች የተለያየ መጠን ያላቸው ክብደቶችና የኤሮቢክስ መስሪያ ቦታዎችን ሁሉ ተሸክሞ ተጠቃሚውን የሚጠባበቅ ሰፊ ክፍል ያገኛሉ። እዚህ ክፍል ውስጥ በቂ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ማድረግ እንዲሁም በፓኬጅ ደረጃ ለወር ለሶስት ወር ልግማሽና ለሙሉ ዓመት ቢፈልጉ የስፓ አገልግሎትን በፓኬጅ በማካተት አገልግሎቱን ማግኘት ይችላሉ።

ሲኒማ

ጋስት ሶላር ህንፃ እሰከ 236 ሰዎች የመያዝ አቅም ያላቸው የዶልብ የድምፅ ሲስተምና የ2D ም ሆነ የ3D ፊልሞችን ማሳየት የሚችሉ ሁለት ሲኒማ ቤቶች አሉት ሲኒማዎቹ በምቹ መቀመጫዎችና በአስገራሚ የድምፅ ጥራት የተደራጁ ሲሆን ከነዚህ በተጨማሪ ደግሞ በአዲስ ሁኔታ ሁለት እሰከ አስራ ስድስት ሰው ብቻ የሚይዙ የግል ሲኒማ ክፍሎች አሉት እነዚህ የጎልድ ሲኒማዎቹ በግል በማስያዝ ከቤተሰብዎ ወይም ከጓደኞችዎ ጋር ሊዝናኑባቸው የሚችሉ ሲሆን ሙሉ ለሙሉ ሌዘር የለበሱት ምቹ ወንበሮች ከወንበርነታቸው ባለፈ የእርስዎ የመዝናኛ አካል መሆናቸውንም ይረዳሉ። በወንበሮቹ መደገፍያዎች ላይ የሚያስቀምጧቸውን መጠጦች ማቀዝቀዝ ከሚችሉባቸው አማራጮች ጀምሮ ተጨማሪ የምስተንግዶ ትእዛዞችን ለማግኘት ካሉበት ሳይነሱ አስተናጋጆች እንዲመጣልዎት መጥራት ይችላሉ። በነዚህ ወንበሮች ላይ ብቻዎ ቁጭ ብለው ካስፈለገም የወንበሮቹን አቀማመጥ በማስተካከል ተንጋለው ፊልም ተዝናንተው እንዲመለክቱ ያስችልዎታል።

ምግብና መጠጥ

በሕንፃው የመሬት ወለል ላይ ከሚገኙት ካፍቴሪያዎች እና ሱቆች እንዲሁም ወደ ላይ ሲወጡ ከሚያገኙት ማይ በርገር በተጨማሪ ህንፃው ላይ የየካን ጋራ እና ጫካ እያዩ የሚበሉበት እና የጠጡበት ሬስቶራንት ተዘጋጅቷል። ከዚህ ውጭ ደግሞ የስፖርት ወዳጅ ከሆኑና የተለያዩ ወድድሮችን እየተመለከቱ መዝናናት ካማረዎ ደግሞ ወደ ስፖርት ባር ጎራ ማለት ይቻላል። በሁሉም አቅጣጫዎች ቢዞሩ የቴልቭዥን ስክርኖችን እየተመለከቱ በባሩ ውስጥ ያሉት የሙድ መብራቶች ዘና ሊሉባቸው ይችላሉ።



መዋዋቢያ

በሰፊው የተሰናዱ በሁለት ወለሎች ላይ የሚገኙት የወንዶችና የሴቶች የመዋቢያ ቦታዎች ላይ ደግሞ ራስዎን ማሳመር ብሎም የቪ አይ ፒ ልምዱን ማየት ከፈለጉም በተለዩ ክፍሎች የማሳጅ የጥፍርና የፀጉርዎን ማሳመር ሥራ በባለሙያች ሊያገኙ ይችላሉ

ሰው የሚጠሩበት ዝግጅት አለዎት?

ጋስት ህንፃ 240 ሰዎችን አሳምሮ የሚያስተናግድ ሰፊ ቦታም አዘጋጅቷል።

#ልዩ_ዳሰሳ

በጋስት ኢንተርቴይመንት ሞል ላይ ያየናቸውን እያንዳንዱን ነገሮች እንዳንገልፅ የገፃችን ብዛት ይገድበናል ነገር ግን ይህ ከ 600,000 የኢትዮጵያ ብር በላይ የወጣበት ህንፃ ለመዝናናት በማንኛውም መስክ ለሚመጡ ሁሉ ተስማምቶ የተሰራ ነው በመሆኑም



#ልዩ_ዳሰሳ

በርካት ብለው ቢሄዱ ማንም ሳይከፋ ያሉትን መገልገያዎችን ሁሉ በየራስ ፍላጎት አሟልተው ሊወቱንበት የሚችሉበት ሞል ነውና ብጎበኙት እንደማይከፉበት እንተማመናለን። ሲ ኤም ሲ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በፈለጉት ሰዓት ቢመጡ 24 ሰዓት ሳይዘጋ አገልግሎት ለመስጠት ዝግጅቱን ባጠናቀቀው የጋስት ሞል አገልግሎቶች ተዝናንተው እንደሚያተርፉ እርግጠኞች ነን።



ዮሐና

በአዲስ አልበም



#አዲስ

ውልደቱ ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት በምትገኘው ደብረዘይት እድገቱ ደግሞ አዲስ አበባ ሲሆን ለሙዚቃ ፍላጎት ማሳየት የጀመረው ገና በልጅነቱ ነው። ከ4 ዓመታት የከፍተኛ ትምህርት ቆይታ በኋላ ሙዚቃ እንደመተዳደሪያ በማረግ በተለያዩ መድረኮች ላይ የሬጌ ስልት ያላቸውን ሙዚቃዎችን ከተለያዩ ባንዶች ጋር በመሆን በምሽት ክበቦች፣ ፌስቲቫሎች፣ ኮንሰርቶች ላይ በማቀንቀን ጀምሯል። ህዝብ ዘንድ በይበልጥ ያስተዋወቀው አዲስ አበባ ላይ በሚደረጉ አለም አቀፍ የሬጌ ሙዚቀኞ የሚገኙበት ኮንሰርቶች ላይ በማቀንቀን በተለየም የሬጌ ሙዚቃ አድማጭ ጋር እውቅናን አገቷል። አለም አቀፍ የሬጌ ስልት አቀንቃኞች ጋር በመድረክ ላይ ለመስራት እድሉን ካገኛቸው ሙዚቀኞች መካከል እንደ JESSE ROYAL፣ PROTIJE፣ CHRONIX ይገኙበታል። ምርጫ አላት የተሰኝውን ስራው ህዳር ወር ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ለህዝብ ማድረስ ችሏል።

በሙሉ ስሙ ዮሃና አሸናፊ እየተባለ የሚጠራው የሬጌ፣ ዳንስ ሆልና አፍሮ ቢት ስልቶች አቀንቃኝ ሙዚቀኛ በእነዚህን የሙዚቃ ስልቶች ትልቅ ቦታ ላይ ይደርሳሉ ተብለው ከሚጠበቁ የሃገራችን ወጣት ድምጻዊያን መካከል አንዱ ነው። ዮሃና



#አዲስ

በራሱ ስም ስያሜ የሰጠውን የመጀመሪያ አልበሙን ጥር ወር ላይ የሙዚቃ ገበያ በማቀላቀል ለሙዚቃ አፍቃሪያን ማድረስ ችሏል። አልበሙ ላይ በአጠቃላይ 10 ሙዚቃዎች የተካተቱበት ሲሆን ሁሉንም ስራዎች ግጥም ራሱ ዮሃና ሰርቷቸዋል። አልበሙ ላይ ከተካተቱት 10ሩ ስራዎች በተጨማሪ በርካታ ያለቀላቸው ስራዎች እንዳሉት የሚናገረው ዮሃና በቀጣይ እንደ እቅድ በየ 2 ዓመቱ አልበም ስራዎች ለህዝብ ለማድረስ እንዳሰበ ይናገራል። የአልበምሙ የመጀመሪያ እትም ሙሉ በሙሉ ያለቀሲሆን የተለያዩ የሃገራችን ከተሞች መድረስ ባለመቻሉና በአድናቂዎች ጥያቄ መሰረት ሙሉ አልበሙን በራሱ የ ማህበራዊ ትስስር ገጾቹ ላይ በነጻ ማቅረቡን ተናግሯል።

የዮሐናን ሙዚቃዎች በነጻ ለማኘት

እዚህ ይጫኑ


ገሞጣ

የፊልም ሽልማት

ለሰድስተኛ ጊዜ



#ናፍቆት



በኢትዮ ፊልም ኋላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አዘጋጅነት በ 2006 ዓ ም በሃገራችን የመጀመሪያ የቀለም ፊልም ስያሜ በመስጠት የሃገራችንን የፊልም ዘርፍ ለማበረታታት የተጀመረ የፊልም ሽልማት ውድድር ነው። የጉማ ፊልም ሽልማት ከመስከረም እስከ ጷግሜ በሃገራችን ላይ ለዕታዩ የበቁ ፊልሞችን እንዲወዳደሩ እድል በመስጠጥ የፊልም ሽልማት ውድድሩን ያካይዳል። ጉማ ፊልም ሽልማት ባደረጋቸው የ5 ዓመታት የሽልማት ውድድሮች ከዓመት ዓመት የውድድር ዘርፉን በማስፋት ባሳላፍነው ዓመት በተደረገው ውድድር በ 18 ዘርፎች ሽልማትን ሰቷል። በተጨማሪም የ5 ዓመታት የሽልማት ፕሮግራሞቹ አለም አቀፍ የሽልማት ውድድሮች ላይ የሚታዩ ሁነቶችን ወደሃገራችን በማምጣት ሃገራዊ እንዲመስል በማድረግ ይታወቃል። ከነዚህም ውስጥ የምንጣፍ ስነ ስራዓት፣ ተወዳዳሪዎች፣ ውድድሩን ለመታደም የሚመጡ ተጋባዝ እንግዶች በአማረ አለባበስ በተለይም በኢትዮጰያዊ በሆኑ አልባሳት አሸብርቀው እንዲመጡ በመጋበዝ ምርጥ አለባበስ ለብሰው ለመጡ ታዳሚያን ሽልማት በማበርከት ለሃገራችን ፋሽን ኢንድስትሪ የራሱ የሆነ እገዛ በማድረግ የተሳካ ስራን ሰርቷል። ባሳለፍነው አመት በተደረገው አምስተኛው የጉማ ፊልም ሽልማት ታዛ የተሰኘው ፊልም በስድስት ዘርፎች የእግዜር ድልድይ የተሰኘው ፊልም በአራት ዘርፎች በማሸነፍ ቀዳሚ ሲሆኑ አርቲስት መሰረት መብራቴ ና ካሣሁን ፍስሃ ማንዴላ በ አምስተኛው ጉማ ፊልም ሽልማት ከታደሙት ታዳሚያን መካከል ድንቅ የሆነ አለባበስ በመልበስ ቀዳሚ በመሆን ተመርጠዋል።

የስድተኛው የጉማ ፊልም ሽልማት ውድድር መጋቢት 17 2011 ከቀኑ 11 ጀምሮ በብሔራዊ ትያትር አዳራሽ ይደረጋል። ባለፉት 5 ዓመታት እንድተደረገው ሁሉ በ 2010 ዓም ከመስከረም እስከ ጷግሜ ለእይታ የበቁ ፊልሞችን ለውድድር ጋብዟል።ባሳለፍነው አመት ሃገራችን ላይ ለዕይታ የበቁ ፊልሞች 61 ገደማ ሲሆኑ ከ61 ፊልሞች ውስጥ 25 የሚሆኑ ፊልሞች ለስድስተኛው የጉማ ፊልም ሽልማት ለውድድር ቀርበዋል። የጉማ ፊልም ሽልማት



ውድድር በ 6ተኛው ውድድሩ እንደ ባለፈው አመት ውድድሩ በተመሳሳይ በ18 ዘርፎች ሽልማቱን ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል። ከነዚህ ውስጥ 1ኛው ዘርፍ ውድድር ሳይሆን የህይወት ዘመን ተሸላሚ እጩ በማደረግ ምስጋና እና እውቅና የሚሰጥበት ዘርፍ ሲሆን ለስድስተኛው የጉማ ፊልም ሽልማት ለውድድር የህይወት ዘመን ተሸላሚ ለመሆን በእጩነት የተመረጡት እውቁና አጋፋው የፊልም ባለሙያ ፕሮፌሰር ሃሌ ገሪማ መሆናቸውን የጉማ ፊልም አዘጋጆች ገልጸዋል። ጉማ ፊልም ሽልማት በዋና ስፖንሰሩ ስም ስያሜ የሰጠው የበደሌ እስፔሻል ምርጥ የተመልካች ፊልም የተሰኘው ዘርፍ ጉማ ፊልም የመካነ ድር በመግባት የፊልም ተመልካቹ ድምጽ ይሰጣል በዚህም መሰረት የ6 ጉማ ፊልም ሽልማት የበደሌ ስፔሻል ምርጥ የህዝብ ምርጫ ፊልም እጩዎች ድንግሉ፣ ሞኙ ያራዳ ልጅ 4፣ ሚስቴን ዳርኪት፣ በእናት መገድ፣ ሃ እና ል 2 በመሆን ምርጥ 5 ውስጥ መካተት ችለዋል። በህዝብ ድምጸ ከሚሰጠው ዘርፍ ውጪ በተቀሩት 17 ዘርፎች በባለሙያ ተዳኝተው ለሽልማት የሚበቁ ይሆናል። በስድስተኛው ጉማ ፊልም ሽልማት ላይ ውሃ እና ወርቅ፣ ወደ ዋላ እና ሲመት የተሰኙት ፊልሞች በ9 ዘርፍ እጩ በመሆን ቀዳሚነት ስፍራ ይዘዋል። በደሌ እስፔሻል ቢራ ጉማ ሽልማት በዋና አጋርነት ለ5 ዓመታት አብሮ በመቆየት ለፊልሙ ዘርፍ እገዛ አድርጓል። በዘንደሮው በጉማ ፊልም ሽልማት ላይ አዲስ ነገር ሊኖር ከሚችሉት ሁነቶች መካከል በሃገሪቱ አዲስ በወጣው ህግ ምክንያት በጉማ ፊልም ሽልማት ላይ በብሔራዊ ትያትር ቤት አዳራሽ ለመታደም የሚመጡ ታዳሚያን ላይ የእድሜ ገደብ ክልከላ ሊኖር የችላል ተብሎ ይጠበቃል።





አቢሲኒያ ቫይን

ቫይን ለኢትዮጵያ

ቫይን መተግበሪያ (APPLICATION) አገልግሎት የተጀመረው እኤአ 2012 ላይ ሲሆን የቫይን መተግበሪ ተጠቃሚዎች አጫጭር የቪዲዮ ቅንጥብጥቦችን በመስራት እንደ FACEBOOK፣ TWITTER፣ YOUTUBE ያሉ የማህበራዊ ትስስር ገጾች ላይ በማጋራት ሰዎች ይጠቀሙበታል። አብዛኛውን ጊዜ የሚሰሩ የቫይን ቪድዮዎች ከ1 ደቂቃ በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ሲሆኑ የተለያዩ መልክቶች ይተላለፉበታል። የቫይን ቪዲዮ በሌላ የአለማችን ሃገራት የተለመደ ሲሆን የተለያዩ የቫይን ቪዲዎች ውድድሮች በብዛት በማህበራዊ ትስስር ገጾች ይደረጋል። በሃገራችንም ያሉ ወጣቶች በተለይም የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተለያዩ የቫይን ቪዲዎች በመስራት በ ማህበራዊ ትስስር ገጻ ላይ በያጋራሉ።

"ኢትዮጵያ ለዘላለም ትሳቅ" በሚል መሪ ቃል መነሻነት ስለተመሰረተው አቢሲኒያ ቫይን ቡድን በ#ሃገርኛ አምዳችን በትንሹ ልናወጋቹ ወደድን።

ትውውቃቸው የጀመረው ራዲካል ት/ቤት የ 4 ክፍል



ተማሪዎች እያሉ ነው። የ10 ክፍል ተማሪ በነበሩበት ወቅት ትምህርት ቤት ውስጥ በሚገኝው ሚኒ ሚዲያ የተለያዩ ሙዚቃዎች በማጫወት ተማሪዎችን በእረፍት ሰዓት እንዲዝናኑ በማድረግ የማዝናናት ስራቸውን ሀ በለው ጀመሩ። በዚህ ጊዜ ከማህላቸው አቤል የተባለው ጓደኛቸው የተለያዩ የባህር ማዶ የቫይን ቪዲዎችን እያመጣ ያሳያቸው ጀመር። የ 12 ክፍል ተማሪዎች በነበሩበት ወቅት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመግቢያ ፈተና በመሰረቁ የዚህን ክስተት ምክንያት በማድረግ የመጀመሪያ የሆነውን የቫይን ቪዲዮ ለመስራት ችለለዋል። ከዚህ ስራ በኋላ በአቤል ሃሳብ አመንጪነት እነደ ቡድን በመሆን የተለያዩ የስራ ዘርፎችን በመከፋፈል አቢሲንያ ቫይን የተሰኘ ሃገራዊ ስያሜ ለቡደኑ በመስጥ የቫይን ቪሲዎችን መስራት ጀመሩ። አቢሲኒያ ቫይንኖች ሃገራዊ ይዘቶችን በመያዝ የተለያዩ አዝናኝ፣ አስተማሪ የሆኑ አጭጭር የሆኑ ቪሲዎችን በቀልድ እያዋዛ በማህበራዊ ትስስር ገጾች ማጋራት በማህበራዊ ትስስር ገጾች ላይ በርካታ ተከታዮች ማግኘት ችለዋል።

አቢሲኒያ ቫይን አጫጭር ቪሲዲዎች ከመስራት በዘለለ የታወቀ የሙዚቃ ስራ በአስቂኝ መገድ መኮረጅ PARODY በመስራት ይታወቃሉ ። የሃገራችን የሙዚቃ ቪዲዮች መካከል የቴዲዮ የኔ ነሽ፣ ስካት ናቲ ስራ በአስቂኝ መገድ የሰሩ ሲሆን በዚህም ስራቸው ከፍተኛ ተቀባይነት ማግኘት ችለዋል። እውቅናቸው ከተለያዩ ትልልቅ ድርጀቶች ጋር የማስታወቂያ ስራዎች መስራት የሚችሉበትን መገድ እድል ከፍቷል።

አቢሲኒያ ቫይኖችን ለማግኘት

እዚህ ይጫኑ



ምርትና አገልግሎትዎን በዳሰሳ አዲስ የማህበራዊ ገጾችና በዙር ሠላሳ ላይ ያስተዋውቁ።

በእያንዳንዱ እትም

500,000+

ሰዎች ያዩዎታል

ዳሰሳ አዲስ ጎትመትና ማስታወቂያ ኃላ. የተ. የግል ማኅበር

+251 924 312 097

addisaccess@gmail.com

ጉርድ ሾላ፣ ጂ እና ቢ ህንጻ 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 310



ACADEMY AWARD

ኦስካር ወይም የአካዳሚ ሽልማት በመባል የሚታወቀው ዝግጅት በፊልሙ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተለያዩ የቴክኒክና የአርት ስራዎች የሚበርከት ሽልማት ነው። ይህ አመታዊ ዝግጅት በተነቀሳቃሽ ምስሎች አርትና ሳይንስ አካዳሚ አዘጋጅነት የሚቀርብ ሲሆን ዋንኛ አላማው አድርጎ የሲኒማ ስኬቶችን ላስመዘገቡ በአካዳሚው አባላት ድምጽ መሰረት ሽልማቱን ይሰጣል። የዛሬ ዘጠና ዓመት ገደማ በዳግላስ ፌይርባንክስ በተዘጋጀውና 270 ሰዎች በታደሙበት የግል የራት ግብዣ ላይ በ ጆርጅ ስታንሊ አዘጋጅነት በሆሊዉድ ሩዜቬልት ሆቴል ተካሂዷል። የሽልማቱ ዝግጅት ለመጀመሪያ ጊዜ በራዲዮ ለመቅረብ የበቃው በ1930 ሲሆን ለአቅመ ቴሌቪዥን ግን ለመድረስ ከዚያ በኋላ 23 ዓመታትን ፈጅቶ በ1950 ነበር። የዚህ ሽልማት መካሄድ መጀመር ለሌሎችም ዘርፎች አርአያ ለመሆን በመብቃቱ ለቴሌቪዥን ዝግጅቶች፣



የኤሚ ሽልማት፤ ለቴአትር፣ የቶኒ ሽልማት እንዲሁም ለሙዚቃው ዘርፍ፣ የግራሚ ሽልማት መጀመር ምክንያት ለመሆን በቅቷል።

በመጀምሪያው የዚህ የአካዳሚ ሽልማት ላይ አሸናፊዎች ማን እንደሆኑ ሦስት ወራት ቅደም ተብሎ ለህዝብ ይፋ የተደረገ ሲሆን ዝግጅቱ የእውቅና ዋንጫ በማበርከት ላይ ብቻ ያተኮር ነበር። በዚህ ዝግጅት እንዲሁም በኦስካር ታሪክ የመጀመሪያው ተሸላሚ በመሆን በምርጥ አርቲስት ዘርፍ ኤሚል ጃኒንግ በታሪክ መዝገብ ላይ ስሙን ያሰፈረ ሲሆን ይህንን ክብር በወቅቱ አዲስ በነበሩት "The last Command" እና "The way of all flesh" በተሰኙት ፊልሞቹ ምክንያት ተቀዳጅቷል።

ይህ በተለያዩ ፊልሞች ምክንያት ለአንድ ዘርፍ የመታጨት ሂደት እስከ ሦስተኛው የኦስካር ሽልማት ድረስ የቀጠለ ሲሆን ከአራተኛው ዝግጅት ጀምሮ ግን ይህንን ልማድ በመሻር እያንዳንዱ አርቲስት በአንድ ፊልማ ላይ በአንድ ዘርፍ ብቻ እንዲታጭ የሚያስገድደውና እስካሁንም ድረስ የዘለቀው ህግ ተግባራዊ እንዲደረግ ሆኗል።

ማርች 29፣ 1957 በተካሄደው 29ኛው ሽልማት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ምርጥ በውጪ ቋንቋ የቀረበ ፊልም የሚል ዘርፍ የተዋወቀ ሲሆን እስከዚያ ጊዜ ደረስ ግን የውጪ ፊልሞች የልዩ ስኬት ሽልማት ብቻ እንዲሰጣቸው ይደረግ ነበር። ከ1973 ጀምሮ ሁልጊዜ የአመቱ ምርጥ ተንቀሳቃሽ ምስልን በመሸለም የሚጠናቀቀው ዝግጅት ከ74ኛው ሽልማት ጀምሮ ደግሞ ለምርጥ የአኒሜሽን ፊቸር ሽልማት መስጠትንም በዝግጅቱ ውስጥ አካትቷል።

ዘጠና አንደኛው የኦስካር ሽልማት ዝግጅት በ2018 ዓ.ም. የተሰሩ ምርጥ ፊልሞችን እውቅና በመስጠት ፌብሩዋሪ 24፣ 2019 ሎስ አንጀለስ፣ ካሊፎርኒያ በሚገኘው የዶልቢ ቴአትር የተከናወነ ሲሆን በኤቢሲ ቴሌቪዥን




የቀጥታ ስርጭት ሽፋን ነበረው። እስከ ዘጠናኛው የአካዳሚው ሽልማት ድረስ 3፣072 የኦስካር ዋንጫ ሽልማቶች ተላልፈዋል።

በዚህ ሽልማት የሚሰጠው ዋንጫ ወይም የኦስካር ሃውልት በወርቅ በተለበጠ ነሃስ ተዘጋጅቶ በጥቁር የብረት መቀመጫ ላይ የሚሰራ ሲሆን 34.3 ሣ.ሜ ከፍታ እና 3.85 ኪሎ ግራም ክብደት ያለው ነው። በዚህ የሃውልት ቅርጽ ላይ የመስቀል ጦረኞችን የሚመስል ሰይፍ አምስት ጫፎች ባሉት የፊልም ጥቅል ላይ ቆሞ ሲታይ አምስቱ ጫፎች አምስቱን ኦሪጅናል የአካዳሚውን ቅርንጫፎች ማለትም ተዋንያን፣ ጸሐፊዎች፣ ዳይሬክተሮች፣ ፕሮዲዩሰሮችና ቴክኒሻኖች ኢንዲወክል ታስቦ የተቀረጸ ነው። በዋንጫው ላይ ያለው የሰው ምስል በሜክሲኳዊው ተዋናይ ኤሚሊዮ "ኤል ኢንዲዮ" ፈርናንዴዝ መልክ እንደተቀረጸ የሚነገር ሲሆን ቀራጺው ጆርጅ ስታንሌይ የሴድሪክ ጊቦንስ ዲዛይን የሆነውን ይህንን ዋንጫ ግዘፍ አካል ሰጥቶታል።

ኦስካር የሚለው የፕሮግራሙ ስያሜ መነሻ አሁንም ድረስ አከራካሪ ነው። የቀድሞ የአካዳሚው ፕሬዚዳንት የነበረችው ቤቲ ዳቪስ በግለ ታሪክ መጽሃፏ ላይ ሽልማቱን የባንድ መሪ በነበረው የመጀመሪያ ባሏ ሃርሞን ኦስካር ኔልሰን እንደሰየመችው ስትናገር በብዛት ግን የሚተርከው ታሪክ ከዚህ በተጻጻሪው የስያሜው መፍለቂያ የአካዳሚው ዋና ጸሃፊ የነበረችው ማርጋሬት ሀሪክ በ1931 ለመጀመሪያ ጊዜ ዋንጫውን በተመለከተች ሰዓት ሀውልቱ በቅጽል ስሙ "አጎት ኦስካር" ብላ የምትጠራው የአጎቷ/የአክስቷ ልጅ የሆነውን ኦስካር ፒርስ እንዳስታወሳት መናገሯ መሆኑን ይናገራል። ነገር ግን አካዳሚው ኦስካር የሚለውን ስያሜ ለሽላቶቹ መጠሪያ እንዲሆነው በይፋ የተቀበለው በ1939 ሲሆን ከዚያ አምስት አመታት ቀደም ብለው እንደ ታይም መጽሄት ያሉ ዋና ሚዲያዎች ስያሜውን መጠቀም ጀምረው ነበር።

የኦስካር አሸናፊዎች ማንነት መረጃ አፈትልኮ





እንዳይወጣ ሲባል ለአሸናፊዎቹ የሚሰጡት ዋንጫዎች የአሸናፊዎቹ ስም ያልተጻፈባቸው የነበሩ ሲሆን ከበዋንጫዎቹ ላይ አይጻፍም። እስከ 2010 ድረስ አሸናፊዎቹ ከዝግጅቱ በኋላ ዋንጫዎቻቸውን በመመለስ ለሳምንታት ያህል ስማቸው በዋንጫዎቹ ላይ ተቀርጾው እስኪመለሱ ድረስ መጠበቅ ነበረባቸው። ከ2010 በኋላ ባሉት አመታት ግን ስም ያለመጻፉ ሂደት እንዳለ ቢቀጥልም ከዝግጅቱ በኋላ በኢለቱ በ"ገዢው አዳራሽ" በሚደረግ ፓርቲ ላይ ወዲያውኑ ስማቸው የተቀረጸበት መደብ በዋንጫዎቻቸው ላይ ማስለጠፍ የሚችሉበት እድል ተመቻችቶላቸዋል። ይህ ሊሆን የቻለው አር ኤስ ኦውንስ የተባለው ድርጅት ሊያሸንፉ የሚችሉ ሰዎችን ስም በበርካታ መደቦች ላይ ቀርጾ በፓርቲው ላይ የሚጠብቃቸው በመሆኑ ነው።

ለአሸናፊዎቹ የሚበረከቱት ዋንጫዎች ባለቤትነት የአሸናፊዎቹ ወይም የወራሾቻቸው መሆኑ እንደተጠብእቀ ቢሆንም እነዚያን ዋንጫዎች ለመሸጥ ቢፈልጉ ግን በቅድሚያ አካዳሚው በአንድ የአሜሪካን ዶላር



እንዲገዛቸው መጠየቅ ይኖርባቸዋል። ይህ ካልሆነ ግን ለማንኛውም ሰው መሸጥ እንዳይችሉ በህግ ይገደዳሉ። ነገር ግን ይህ አሰራር ህጋዊ ሆኖ መተግበር የጀመረው በ1950 በመሆኑ ከዚያ ቀደም የተላለፉ ሽልማቶች በዚህ ህግ የማይገዙ በመሆናቸው በታሪክ ውስጥ የተወሰኑ የኦስካር ሽልማቶች በጨረታ ለሽያጭ ቀርበው በከፍተኛ ዋጋ ተሸጠዋል።

የተንቀሳቃሽ ፊልሞች አካዳሚው ለዎች ፊልሞች ከሚሰጣቸው የእውቅና ሽልማቶች በተጨማሪ ዘነኝ የተለያዩ የክብር ሽልማቶችን ያበረክታል። እነዚህ ሽልማቶች የአካዳሚ የክብር ሽልማት፣ የኢርቪን ጊ ታልበርግ መታሰቢያ ሽልማት፣ የጂን ሄርስሆልት የሰብአዊነት ሽልማት በገዢዎች ሽልማት ዝርዝር ውስጥ የሚካተቱ ሲሆኑ በሳይንቲፊክና ቴክኒካል ሽልማት ዘርፍ ስር ደግሞ የአካዳሚው ሜሪት ሽልማት፣ የሳይንቲፊክና ምህንድስና ሽልማት፣ የቴክኒካል ስኬት ሽልማት፣ የጆን ኤ ቦነር የኮንዴሽን ሜዳልያ፣ የጎርደን ኢ ሳውየር ሽልማት እንዲሁም የተማሪዎች አካዳሚ ሽልማት በአካዳሚው የሚሰጡ ተጨማሪ ሽልማቶች ሆነው ይሰጣሉ።



የዝግጅቱ ሥም፡ THE OSCARS

የአየር ላይ ቆይታ፡ 89 ዓመታት

የተሰጡ ሽልማቶች፡ >3,000

የተላለፈባቸው ቲቪዎች፡ NBC

(እ.ኤ.አ 1953-1960 ዓ.ም.)

ABC

(እ.ኤ.አ 1961-1970 ዓ.ም.)

NBC


(እ.ኤ.አ 1971-1975 ዓ.ም.)

ABC

(እ.ኤ.አ 1976 ዓ.ም. እስከ አሁን)



Oscars Website



#ፊልሞች

አትፍረድ

ቆይታ: 1:35
ዘውግ: ልብ አንጠልጣይ
ፅሃፊ: ፍፁም አስፋው
ዳይሬክተር: ፍፁም አስፋው
ፕሮዲዩሰር: እስከዳር አስፋው
ተዋንያን: አለማየሁ ታደሰ፣ ፀደይ ፋንታሁን፣ አለምሰገድ አሰፋ



ባለ ጊዜ

ቆይታ: 1:45
ዘውግ: ድራማ
ፅሃፊ: ብርሃኑ ወርቁ
ዳይሬክተር: ብርሃኑ ወርቁ
ፕሮዲዩሰር: ብርሃኑ ወርቁ
ተዋንያን: መኮንን ላዕከ፣ እንግዳሰው ሀብቴ፣ ዓለማየሁ በላይነህ፣ ፌቨን ከተማ፣ ብርሃኑ ወርቁ



ከፍሎ ሚች

ቆይታ: 1:40
ዘውግ: ድራማ
ፅሃፊ: አብዲሳ ምትኩ
ዳይሬክተር: ተክሉ ኡርጋ
ፕሮዲዩሰር: ተክሉ ኡርጋ
ተዋንያን: ዓለማየሁ ታደሰ፣ ሄለን በድሉ፣ ፍቅርተ ደሳለኝ ዓለማየሁ በላይነህ